| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "ዜና ፡ ስሌት ። " |
| ርእስ ፤ | "5G ፡ ወይም ፡ 5 ኛ ፡ ትውልድ ፡ እና ፡ እኹል-ገብ ፡ ኢንተርኔት ። " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-003 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ዜና ፡ ስሌት ።

Computing News | Nouvelles d'informatique | اخبار العقل

## የ"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ መርበቢያ ፡ awdeqelem.net ፡ ከነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ አላግባብ ፡ ታግዷል ።

"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ የተባለው ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ መርበቢያ ፡ awdeqelem.net ፡ ከነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ መታገዱን ፡ ባለቤቱ ፡ አቶ ፡ ወሌ ፡ ነጋ ፡ ገልጸውልናል ።

የታገደበትን ፡ ምክንያት ፡ ሲያብራሩ ፥ የመርበቢያው ፡ አከራይ ፥ ፈረንሳዊው ፡ ድርጅት ፡ Groupe Magic Online ፡ ባሳየው ፡ ያገልግሎት ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፥ ለሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ ደንበኝነታቸውን ፡ እንደማይቀጥሉ ፡ አሳውቀውት ፥ ከሌላ ፡ አከራይ ፡ ጋራ ፡ በሚነጋገሩበት ፡ ወቅት ፥ የኪራዩ ፡ ዘመን ፡ ከማለቁ ፡ 2 ፡ ወራት ፡ በፊት ፥ Groupe Magic Online ፡ (https://magic.fr) ፡ የመጨውን ፡ ዓመት ፡ ኪራይ ፡ አለፈቃዳቸው ፡ ከባንክ ፡ ሒሳባቸው ፡ ወስዶ ፥ ገንዘቡንም ፡ መልስ ፡ እንዳይባል ፥ መርበቢያቸውን ፡ ላልጠየቁት ፡ ለሌላ ፡ አከራይ ፡ አኹንም ፡ አለፈቃዳቸው ፡ በማዛወሩ ፡ በተፈጠረ ፡ ውዝግብ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

አኹን ፥ ጕዳዩ ፡ የመርበቢያዎችን ፡ ስም ፡ ምዝገባና ፡ ጠቅላላ ፡ ጕዳይ ፡ በበላይነት ፡ ለሚመለከተው ፡ ለ ICANN ፡ ስለ ፡ ቀረበ ፥ ከምርመራ ፡ በኋላ ፡ የሚሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ እንደሚጠባበቁ ፡ ገልጸውልናል ።

Groupe Magic Online ፡ የተባለው ፡ ፈረንሳዊ ፡ ድርጅት ፡ የኢ.ሀ.ሥ.አ.ንም ፡ መርበቢያ ፡ (slttunhzb.net) ፡ ለብዙ ፡ ወራት ፡ ማወኩ ፡ ይታወሳል ። ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጕዳዩን ፡ ለፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ የውጭ ፡ ጕዳይ ፡ ምጋቤ ፡ ካቀረበው ፡ በኋላ ፥ መርበቢያውን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አከራይ ፡ ድርጅት ፡ ማዛወሩ ፡ ይታወሳል ።

"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ የተባለውን ፡ መግበር ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ስለሚሠራበትና ፡ ያገልግሎቱንም ፡ ጥቅም ፡ ለሌሎች ፡ ለማስተዋወቅ ፡ ስለ ፡ ወደደ ፥ በባለቤቱ ፡ በአቶ ፡ ወሌ ፡ ነጋ ፡ ፈቃድ ፥ መግበሩን ፡ ማንኛው ፡ ሰው ፡ ከመርበቢያችን ፡ ከ slttunhzb.net ፡ በነጻ ፡ ሊቀዳው ፡ እንደሚችል ፡ እናስታውቃለን ።

የጕዳዩን ፡ አካኼድ ፡ ተከታትለን ፡ በመጪው ፡ ዕትማችን ፡ እንዘግባለን ፨


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።